# ዘመናዊ ትምህርትና ስልጣኔ

በቅርቡ የተከበረው የአድዋ በዓል አገራችን በጊዜው በጦር ሜዳ ከተቀዳጀችው አንፀባራቂ ድል በሁዋላ በአለም አቀፍ ደረጃ ያተረፈችውን ክብርና ዝና የነበራትንም ብሩህ የእድገትና የስልጣኔ ተስፋ እንድናስታውስ ያደርገናል;; ከአድዋ ድል ማግስት መላው የነጭ ዘርና የአውሮፓ መንግስታት ከመቀመጫቸው ብድግ ብለው እንደ እኩል አባላቸው እጅ ነስተው ነበር ኢትዮጵያን የተቀበሉትና ያላችውንም መልካም ምኞት የገለፁት;;

የፓሪሱ መጽሔት “La liberte” ዋና አዘጋጅ በወቅቱ እንዲህ ጽፎ ነበር:- “ All European countries will be obliged to make a place for this new brother who steps forth ready to play in the dark continent the role of Japan in the far east.” (quoted by Robert Hess, Ethiopia: The Modernization of Autocracy) በማለትም ተንብዮ ነበረ ;; ግና ትንቢቱ ሊሰምር እውን ሊሆን አልበቃም;; ኢትዮጵያም እንደ ጃፓን ለምዕራቡ ዓለም ስልጣኔ ስትጋለጥ በተመሳሳይ ስርአተ ማህበርና ሁኔታ ላይ የምትገኝ አገር ብትሆንም ጃፓንን ለመሆን ሳትታደል ቀረች;;

ጃፓንን ከእኛ በተለየ ሁኔታና መንገድ በአጭር ግዜ ውስጥ መጥቀው ትናንትናና ዛሬ ለደረሱበት ደረጃ ያበቃቸው ዋንኛው አስማትና ምትሃት ዘመናዊ ትምህርትን ከአገራቸው አፈርና ከራሳቸው ባህል ጋር ለማዋሃድ የፈጠራ ችሎታችውን ተጠቅመው ስለሰሩበት ነው;; የምዕራቡን ዓለም እውቀትና ቴክኖሎጂ ሲያስገቡ በራሳቸው አምነውና ተማምነው ባህላቸውን ወጋቸውን ማዕከል አድርገው ና ጠብቀው ለዕድገት መጠቀሚያና መገልገያም በማድረጋቸው ነው;;

ያለፉት ትውልዶች መራራና ፈታኝ ወቅትን በታላቅ ድፍረት በቆራጥነትና ግዜሩ በሰጣቸው የማመዛዘንና የፈጠራ ችሎታ ተጠቅመው ይቺን አገር በድል አድዋ ድረስ ካደረሷት ና ከሐያል የአውሮጳ አገሮች ጎን ካስቀመጧት በሁዋላ ዘመናዊ ትምህርት አገራችን ገብቶ በቀጣዩ ትውልዶች የተማረው ቁጥር በዝቶ ባደገ ቁጥር የኢትዮጵያም ችግርና መከራ እየሰፋ ኋላቀርነትና ልመናው እየከፋ ሄዶ እነሆ ዛሬ ከምንገኝበት ደረጃ ላይ ተደርሷል;;

በእሳትና በብረት ያልተንበረከከችው ኢትዮጵያ በዘመናዊ ትምህርት ተጠቅልሎ በገባ የማይታይ መርዝ አንዲት ጥይት ሳትጬህ ተረትታ እነሆ አንድ ምዕተ ዓመት ሙሉ በድህነትና በጉስቁልና ታገግምለች;; የተማሩ ልጆቿም ዐይናቸው የሚያይ ግን የማያስተውል; ጆሮቻቸው የሚሰማ ግን የማያዳመጥ; ልባቸው የሚነሆልል ግን የማይቀርጥ; ክንዳቸው የሚዘረጋ ግን የማይፈረጥም ሆኖ በምዕራብ ስልጣኔ ተጀንጅነውና ተጀንነው ቢረደትም ባይረደትም በእጅ አዙር ቅኝተገዥነት የሚማቀቁ ሆነዋል;;

ከላይ ያነሳሁት የመንደርደሪያ ሃሳብ ዘመናዊ ትምህርት ችግሩ ምኑ ላይ ነው? እነዴትስ የእድገት እንቅፋት መሆን ይችላል? የመሳሰሉትን ጥያቄዎች እነደሚጭር እገነዘባለሁ;;

ዘመናዊ ትምህርት ራሱ በራሱ ምንም ችግር የለበትም ....የሳይንስ እውቀት ክፋት የለውም;; ያለትምህርትም እድገትና ስልጣኔ እነደማይኖር የታወቀ ነው;; ችግሩ ያለው የዘመናዊ ትምህርት ሲገባ አብሮት የሚገባው ከጀርባው ያለው /background/ ላይ ነው;; ችግሩ ያለው የዘመናዊ ትምህርት ፈጣሪና አቀባዩ /agent/ ላይ ነው;; እነደሚታወቀው ዘመናዊ ሳይንስና ቴክኖሎጂን ያበቀለው የአውሮፓ የባህል መሰረት ነው;; (ባህል ስንል የህብረተሰብ ቁሳዊና መንፈሳዊ ህይወት ባጠቃለለ ሰፊ ትርጉሙ) ይህም ባህል ራሱን የሚያይበትና ከሱ የሚለዩትን ባዕድ ባህሎች የሚመለከትበት የራሱ መነጽር አለው;;

በአውሮፓውያን መነጽር /Ideology , Eurocentric concepts / ከአውሮፓ ስልጣኔ ወጭ ያሉ ወይም የነበሩ ስልጣኔዎችና ቅርሶች ሁሉ የበታች ኢምንትና የጊዜን እርጅና የሚያስታውሱ ግውዛን የመልከአ ምድር ምልክቶች ናቸው;; የአክሱምና የጎንደር ስልጣኔ ; የግብጽን ፒራሚዶች ያቆመው ስልጣኔ; የዚምባብዌን ግንብ የገነባው; የፔሩን የቦሊቪያን ሃውልትና ፒራሚዶችን ሰማይ አጣቅሶ የጎለተው ሌሎችም የነጭ ያልሆኑ ትልቅና ትንሽ ስልጣኔዎች በታሪክ ቡቱቶና ድሪቶነት እነዲደነቁ እንጂ ወራሽ ያላቸው ቀጣይነትና ተከታታይነት ሊኖራቸው የሚችል የህያው ህዝቦች ህያው የህይወት ታሪክ እነደሆኑ አያይም አያወሳም;; በዚህ መልክ እንዲታዩና እነዲታወሱ ለራሱም አይፈቅድም;; እነኚህ ህያው የታሪክ አሻራዎች በግውዝነት ሲፈርጁ ከዚህም ጋር አብሮ ከነጩ በስተቀር የተቀረው ካወሮፓ ስልጣኔ ውጭ ያለው የአፍሪካ የእስያ የአሜሪካ ህዝቦች ያልሰለጠኑ /barbaric sub-human / ቅጽል ተሰጥቷቸው መሰልጠንና መገራት እንዳለባቸው ያስተምራል;; ዘመናዊ ትምህርትም የዚህ ባህልና ስልጣኔ አካል እንደመሆኑ የተሰጠው ተልዕኮ በአስፈጻሚዎቹ ነጭ ሚሺነሮች ወይም ቀድመው በነሱ በሰለጠኑ ያካባቢው ተወላጆች እነኚህን ህዝቦች ነፃ ማውጣትና ማሰልጠን ነው;;

ዘመናዊ ትምህርት ተጠቀልሎና ታዝሎ የሚቀርብበት አንቅልባ /background/ በግርድፉ ይህን የመሰለ ሲሆን የተለየ ባህልና ስልጣኔ ያለው አገርና ህብረተሰብ ውስጥ ሲገባና ለግለሰብ ትምህርት ገበታ ላይ ሲቀርብ ይህን አውሮፓዊ አመለካከት /Ideology/ ከትምህርትና ከሳይነሱ ጋር አብሮ የመውሰድ አዳላጭ አደጋ ይፈጠራል;;

ይህ ጠንቃቃ ላልሆነ ዓይን የተሰወረ; ትንሽና ቀላል የመሰለ አደጋ የሚያስከተለው መዘዝና ቀውስ የአገሮችንና የህዝቦችን ዕጣና ዕድል ለከፉ ወይም ለደግ የሚለይ ወሳኝ ምክንያት ሆኗል ;; እንደ ኢትዮጵያ ያለችውን በተፈጥሮ ሃብት በሰው ሃይልና በኢንተለክት የተቸረችዋን አገር አደህይቶ መና ያስቀራል .... ወይም ጃፓንን የመሰለች ቁራሽ አገር የስልጣኔ ኮኮብ እነድትሆን ያደርጋል;;

የሚያሳዝነው ነገር በቅኝ ግዛት ስር የወደቁ አገሮች ይህንን መርዝ በሃይልና በጉልበት እንዲግቱ ሲገደዱ ኢትዮጵያውያን ግን በፈቃዳችን ጨልጥነው ይኸው ድፍን ምዕተ-ዓመት ያሸለብን መሆኑ ነው;; ዛሬ እንኚህ አገሮች እኛም እነሱም ባንድ ሰልፍ በአንድ ተርታ መሰለፋችን ብቻ ሳይሆን ከመጨረሻው የመጀመሪያዎቹ ሆነን እንገኛለን;; የአድዋ ድልም በዚህ ትውልድ ትርጉም አጥቶ በዓሉ የሚከበረው ጀግኖቹን ያን ጎበዝ ትውልድ ለመዘከር ብቻ  ታስቦ የሚውል ነው;;

ከዘመናዊ ትምህርት ጋር አብሮ የሚገባው ታላቁ መርገም  አእምሮን ገንዞ ከትወልድ ትውልድ አኮላሽቶ አገርን የሚያመከነው እጅ አዙር ቅኝ ተገዥነት -ፈረንጅን ማምለክና ራስን ማረከስ -  ከዘመናዊ ትምህርት ጋር የሚመጣው ባጭሩ በዚህ መልኩ ነው;;

ስልጣኔ የነጮች ስራ ; የነጮች ፀጋና በረከት መማር መሰለጠንም ፈረነጆቹን መሆን ማለት ይሆናል;; መሰልጠን ማለት እንደ ፈረንጆቹ ማሰብ ; እነደነሱ ማምረት; በነሱ መሳሪያ መጠቀም በነሱ እምነት ማምለክ በነሱ ቋንቋ መናገር ; እንደነሱ መልበስ ; መዝፈን ;መደነስ ሆኖ ስለሚታመን የፈረንጅ ያልሆነውና ፍፁም የተለየው በሙሉ ያልሰለጠነና  ዝቅተኛ ተደርጎ ይታየል;; በዚህ እምነት  መሰረትም  ራስንም ጨምሮ የራስ የሆነ ነገር በሙሉ ዋጋና ክብር ያጣል;; በመሆኑም ለመስልጠን የመጀመሪያው ርምጃ  ከዚህ "ሁዋላ ቀርነት"- ከራስ ማንነት መገላገል አብይና ተቀዳሚ ተግባር ሆኖ ይቀርባል;; ለዚህም መንገዱ ዘመናዊ ትምህርት ይሆናል;; በውጤቱም የመማር አብይ ዓላማ ዒላማውን ሰቶ የእልፍኝ ከልፍኝ ሙሴዎችን የሚፈለፍል ኢንኩቤተር ሆኖ ቁጭ ይላል;;  ዶ/ር መሳይ  ከበደ ይህንን እውነታ " The Root Cause of Famine " በሚለው መጣጥፉ እንዲህ ይገልፀዋል;- "….If we must become civilized, is it not because  we consider ourselves as a backward, uncivilized? To receive modern education is to transit from primitive life to civilized life. As a process of emerging from a state of sub-humanity, modernization, that is, westernization is how the model, the prototype of human life is dissolves our barbarism."

በመቀጠልም "….modern education is not basically how we learn some techniques and skills to improve our life, more specifically, to catch up with the west in terms of technology so as to preserve our independence and mode of life. No, it is first and foremost how we become real human beings, that is civilized people. One drastic effect of  this self- debasement induced by the normative ness of the west is the addiction to imitativeness. since we are in the business of becoming converts, we don't create: we simply assimilate."

መሰልጠን /modernization-westernization/ የመጀመሪያው እንድምታና  ቅድመ ሁኔታ  የነበረውንና ያለውን የማህበረሰቡን ታሪካዊና ባህላዊ ቅርስና እሴቶች ማድከምና ማድቀቅ ነው;; አዲሱን የውጭውን ስልጡን ባህል በላዩ  ለመተካት ጥርጊያ ጎዳና መክፈት ;; ህብረተሰቡ የቆመበትን መሰረት ከሁሉ በላይ ደግሞ    የማንነቱን ስነ ልቡናዊ ምሶሶ -በራስ መተማመንን- በሽክምነቱና ጎታችነቱ ያለ "ጥርጥርና ምስክር" ከጠዋቱ ተፈርዶበት

**ተገንዞ እንዲቀበር ይደርጋል;; በዚህም የሳይንስ እውቀት ስር ሊሰድበት; የፈጠራ ስራ ሊያብብበት  የአገር ስልጣኔ ሊቆመበት የሚገባው የማዕዘን ድንጋይ ተንዶ; የሚገበየው እውቀት መሰረትና ግድግዳ  የሌለው ጣራ ይሆናል;;**

**ይቀጥላል**

**ጃዊሳ**